የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፲፯
አዲስ አበባ የካቲት ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፰

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32nd Year No. 17
ADDIS ABABA, 23rd February, 2026

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፹፮/፪ሺ፲፰
ለኢንቨስትመንት ስለሚሰጥ የቀረጥና ታክስ ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..... .....ገጽ ፲፱ሺ፭፻፳፰

Content

REGULATION No. 586/2026
For Investment Providing Tax and Customs Incentive Council of Ministers Regulation …….....Page 19528

ደንብ ቁጥር ፭፻፹፮/፪ሺ፲፰

ለኢንቨስትመንት ስለሚሰጥ የታክስና ቀረጥ ማበረታቻ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የገቢ ግብር አዋጅ (እንደተሻሻለ) ቁጥር ፱፻፸፱/፪ሺ፰ አንቀጽ ፩፻፭ በኢንቨስትመንት ሕጉ መሰረት ኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸው ባለሀብቶች ሊሰጣቸው የሚገባው የገቢ ግብር ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ሊወሰን እንደሚገባ የሚደነግግ በመሆኑ፤

የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ (እንደተሻሻለ) ቁጥር ፭፻፲፯/፪ሺ፲፭ አንቀጽ ፯ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንቡ የተቋቋመውን የገቢ ግብር የማበረታቻ ዓይነት በሌላ የማበረታቻ አይነት ሊተካው እንደሚችል የሚደነግግ በመሆኑ፤

REGULATION No. 586/2026

FOR INVESTMENT PROVIDING TAX AND CUSTOMS INCENTIVE COUNCIL OF MINISTERS REGULATION

WHEREAS, pursuant to Article 105 of the Income Tax Proclamation (as amended) No. 979/2016, income tax incentives for investors holding an investment license under the Investment Law shall be determined by Regulations issued by the Council of Ministers;

WHEREAS, Article 7 of Council of Ministers Regulation (as amended) No. 517/2022 on Investment Incentives provides that the Council of Ministers may replace the income tax incentive established under the Regulation with a new incentive system;

የኢንቨስትመንት ማበረታቻው አፈፃፀምን መሰረት ያደረገ እንዲሆን በማድረግ ለኢኮኖሚው እድገት አስተዋጽኦ ላላቸው ከፍተኛ ካፒታል ለሚጠይቁ የኢንቨስትመንት መስኮች እንደየካፒታል መጠኑ ትኩረት በመስጠት ማበረታታት እንዲያስችል ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በዚህም ቅድሚያ በሚሰጣቸው የኢንቨስትመንት መስኮች ላይ ያተኮረ፣ በስራ ላይ የሚውለውን ካፒታል ከግምት ውስጥ የሚያስገባ እና በአፈፃፀም ላይ የተመሰረተ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ስርአት ስራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ማበረታቻዎችን በተመለከተ ተጠያቂነትን ለማጎልበት፣ ከዓለም አቀፍ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር እንዲጣጣም ለማድረግ እና የሚሰጡት ማበረታቻዎች ቀላል እና ግልፅ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹/፪ሺ፲፪ አንቀፅ ፲፯ የገቢ ግብር አዋጅ (እንደተሻሻለ) ቁጥር ፱፻፷፱/፪ሺ፲ አንቀጽ ፩፻፳ እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፱/፪ሺ፮ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፩፻፳፱ ንዑስ አንቀጽ ፮ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

WHEREAS, it has become necessary to make the investment incentive system performance-based, supporting incentives for capital-intensive sectors that contribute to economic growth while considering the capital employed;

WHEREAS, it is necessary to implement a performance-based investment incentive scheme that prioritizes strategic investment sectors, takes into account of capital employed, and ensures that incentives are granted strictly on the basis of measurable performance;

WHEREAS, it is necessary to strengthen accountability in the administration of incentives, ensure alignment with global economic dynamics, and make incentive regimes simple, transparent;

NOW, THEREFORE, the Council of Ministers hereby issues this Regulation pursuant to Article 17 of Investment Proclamation No. 1180/2020, Article 105 of the Income Tax Proclamation (as amended) No. 979/2016, and Article 129 Sub Article 6 of Customs Proclamation No. 859/2014 (as amended).

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "ለኢንቨስትመንት ስለሚሰጥ የቀረጥና ታክስ ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፹፮/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

ለቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ **"የኢንቨስትመንት ማበረታቻ"** ማለት በዚህ ደንብ መሰረት ለማበረታቻ ብቁ ለሆነ ኢንቨስትመንት የሚሰጥ ማበረታቻ ነው፤

፪/ "**የካፒታል ወጪ ተቀናሽ**" ማለት አንድ ኢንቨስትመንት ስራ በሚጀምርበት ወቅት ለካፒታል ንብረቶች ባወጣው ወጪ ላይ በተወሰነ መቶኛ የሚሰላ ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚፈቀድ እና በሰንጠረዥ ፪ መሰረት የሚፈጸም ተቀናሽ ወጪ ነው፤

፫/ **"ኢንቨስትመንት"** ማለት አዲስ ኢንቨስትመንት ወይም የነባር ኢንቨስትመንት ማሻሻያ ወይም ማስፋፊያ ነው፤

PART ONE

GENERAL PROVISIONS

1. Short Title

This Regulation may be cited as the "For Investment Providing Tax and Customs Incentive Council of Ministers Regulation No. 586/2026."

2. Definition

Unless the context requires otherwise, in this Regulation:

1/ "**Investment Incentives**" means the incentives, granted to eligible investment in accordance with this Regulation;

2/ "**Deduction of Capital Expenditure**" means a one-time deduction calculated as a percentage of the cost of capital assets incurred by an investment at the commencement of operations and provided based on in accordance to Table 2 of the Regulation;

3/ **"Investment"** means a new investment or upgrading or expansion of an existing investment;

፬/ **"የአፈጻጸም ስምምነት"** ማለት በባለሀብቱ እና አግባብ ባለው የኢንቨስትመንት ወይም በማዕድን ጉዳይ ላይ ኃላፊነት በተሰጠው የመንግሥት መሥሪያ ቤት መካከል በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፮ በተመለከተው መሰረት የሚደረግ ውል ነው፤

፭/ **"ከመደበኛው ያነሰ"** ማለት በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፱/፪ሺ፰ (በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፺፭/፪ሺ፲፯ እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፲፱ መሰረት በንግድ ስራ ገቢ ላይ ተፈጻሚ ከሚሆነው መደበኛ የማስከፈያ መጣኔ ያነሰ እንደ ልዩ ማበረታቻ ለባለሀብቶች ተፈጻሚ የሚሆን የንግድ ሥራ ገቢ ግብር የማስከፈያ መጣኔ ነው፤

፮/ **"አዋጅ"** ማለት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹/፪ሺ፲፪ ነው፤

፯/ **"ካፒታል"** ማለት የአገር ውስጥ ወይም የውጭ ገንዘብ፣ የሚተላለፍ ሰነድ፣ የማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ መሳሪያ፣ ህንጻ፣ የሥራ ማስኬጃ ካፒታል፣ የንብረት መብት፣ የአዕምሯዊ ንብረት መብት ወይም ሌላ የሚዳሰስ ወይም የማይዳሰስ የንግድ ሀብት ነው፤

፰/ **"የካፒታል ዕቃ"** ማለት ለሽያጭ የሚውሉ ምርቶችን ለማምረት ወይም አገልግሎቶችን ለመስጠት ጥቅም ላይ የሚውል፣ ከአንድ ዓመት ላላነሰ ጊዜ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው መሣሪያን እና እነዚህን የመሳሰሉ ግዙፋዊ ሀልዎት ያላቸውን ሌሎች ንብረቶች ይጨምራል፤

4/ "**Performance Agreement**" means a legally binding contract concluded between an investor and the relevant investment or the government institution mandated for mining activities pursuant to Article 26 of this Regulation;

5/ **"Reduced from the Regular"** means a reduced business income tax rate granted to an investor as a special incentive, set below the regular rate applicable to business income pursuant to Article 19 of Income Tax Proclamation No. 979/2016 (as amended by Proclamation No. 1395/2025);

6/ **"Proclamation"** means Investment Proclamation No. 1180/2020;

7/ **"Capital**" means domestic or foreign currency, negotiable instruments, machinery or equipment, buildings, working capital, property rights, intellectual property rights, or any other tangible or intangible business assets;

8/ "**Capital Good**" means equipment or similar tangible assets used to produce goods or render services for consideration, with a useful economic life of not less than one year;

፱/ “**ማምረት**” ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የኢንዱስትሪ ሂደትን በመጠቀም ጥሬ ዕቃ ወይም ግብአት በምርት ሂደት ውስጥ በማሳለፍ፣ በማቀናበር ወይም ቅርጹን ወይም አገልግሎቱን በመለወጥ ሌላ አዲስ መጠሪያ ወይም ባህሪ እና ጠቀሜታ ያለው ዕቃ ማውጣት ሲሆን ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወስናቸውን ሙሉ ለሙሉ ተበታትነው ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎችን መገጣጠምን ሊጨምር ይችላል፤

9/ “**Manufacture**” means the industrial production of goods through processing, transforming, or altering the form or function of raw materials or inputs in Ethiopia to produce goods with new characteristics, name, or value and includes the assembly of goods imported in completely knocked-down form, as determined by the Ministry in a Directive;

፲/ “**የግንባታ ዕቃ**” ማለት የህንጻ ወይም የግንባታ ስራ አካል የሚሆን ለግንባታ ሥራ የሚውል ዕቃ ነው፤

10/ “**Construction Material**” means any material intended to be incorporated into a building or other construction;

፲፩/ “**ልዩ የኢኮኖሚ ዞን**”፤ “**የልዩ የኤኮኖሚ ዞን አልሚ**”፤ “**የልዩ የኤኮኖሚ ዞን ንኡስ አልሚ**”፤ እና **የልዩ የኤኮኖሚ ዞን ድርጅት**” የሚሉት ሃረጎች በልዩ የኢኮኖሚ ዞን አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፳፪/፪ሺ፲፮ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፤

11/ The terms “**Special Economic Zone,**” “**Special Economic Zone Developer,**” “**Special Economic Zone Sub-Developer,**” and “**Special Economic Zone Enterprise**” shall have the meanings assigned under Special Economic Zone Proclamation No. 1322/2024;

፲፪/ “**ስታርታፕ**” እና “**የስታርታፕ ምኅዳር ገንቢ**” የሚሉት ቃላት በስታርታፕ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፣፻፺፮/፪ሺ፲፯ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፤

12/ The terms “**Startup**” and “**Startup Ecosystem Builder**” shall have the meanings assigned under Startup Proclamation No. 1396/2025;

፲፫/ **"ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት"** ማለት የኢንቨስትመንት ተቋማት፣ የማዕድን ሚኒስቴር፣ የማዕድን ቢሮዎች፣ የቱሪዝም ሚኒስቴር፣ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ የታክስ ባለስልጣን፣ የጉምሩክ ኮሚሽን እና ሌሎች የኢንቨስትመንት ማበረታቻ አፈፃፀምን ለመቆጣጠር በሕግ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ናቸው፤

13/ "**Regulatory Institutions**" means investment institutions, the Ministry of Mines, Mining Bureaus, Ministry of Tourism, the Ministry of Trade and Regional Integration, the Tax Authority, the Customs Commission, and any other institution legally mandated to regulate the implementation of investment incentives;

፲፬/ **"የኢንቨስትመንት ተቋም"** ማለት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ ከኮሚሽኑ የውክልና ስልጣን የተሰጠው የፌደራል መንግስት አካል፣ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ወይም ኢንቨስትመንት ለማስተዳደር ስልጣን የተሰጠው የክልል እና የከተማ አስተዳደር አካል ነው፤

14/ **"Investment Institution"** means the Ethiopian Investment Commission, any Federal entity delegated by the Commission, or a Regional Government or city administration authority empowered to issue investment permits or administer investment operations;

፲፭/ **"የታክስ ባለስልጣን"** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም የክልል መንግሥታት እንዲሁም የድሬዳዋ እና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድሮች የገቢዎች ቢሮዎች ናቸው፤

15/ **"Tax Authority"** means the Ministry of Revenue or the Revenue Bureaus of Regional Governments and the Dire Dawa and Addis Ababa City Administrations;

፲፮/ **"አማራጭ አነስተኛ ግብር"** ማለት በገቢ ግብር አዋጅ (እንደተሻሻለ) ቁጥር ፱፻፸፱/፪ሺ፰ አንቀጽ ፳፫ መሰረት የተጣለው ግብር ነው፤

16/ **"Minimum Alternative Tax"** means the tax imposed pursuant to Article 23 of the Income Tax Proclamation No. 979/2016 (as amended);

፲፯/ **"በትርፍ ድርሻ ላይ የሚከፈል ግብር"** ማለት የገቢ ግብር አዋጅ (እንደተሻሻለ) ቁጥር ፱፻፸፱/፪ሺ፰ አንቀጽ ፶፯ መሰረት የተጣለው ግብር ነው፤

17/ "**Tax on Dividend Income**" means the tax imposed pursuant to Article 57 of the Income Tax Proclamation No. 979/2016 (as amended);

፲፰/ **"የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ግብር"** ማለት የገቢ ግብር አዋጅ (እንደተሻሻለ) ቁጥር ፱፻፸፱/፪ሺ፰ አንቀጽ ፷፪ መሰረት የተጣለው ግብር ነው፤

18/ **"Capital gains Tax"** means the tax imposed pursuant to Article 62 of the Income Tax Proclamation No. 979/2016 (as amended);

፲፱/ **"የገቢ ግብር"** ማለት በፌደራል ወይም በክልል መንግሥታት የገቢ ግብር አዋጆች በሠንጠረዥ "ሐ" በተመለከተው ገቢ ላይ የተጣለ ግብር ነው፤

19/ "**Income Tax**" means the income tax imposed on Schedule "C" under the Income Tax laws of the Federal or Regional Governments;

፳/ "**የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ማበረታቻ"** ማለት ባለሀብቱ ለኢንቨስትመንቱ አስፈላጊ የሆኑትን የካፒታል ዕቃዎች፣ የግንባታ ዕቃዎች እና ተሽከርካሪዎችን ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው መሰረት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ በመሆን ወይም በአነስተኛ የቀረጥ ማስከፈያ መጣኔ እንዲሁም ከታክስ ነፃ በመሆን ወደ አገር የሚያስገባበት ሥርዓት ነው፤

20/ "**Customs Duty and Tax Incentives"** means a system allowing an investor to import capital goods, construction materials, and vehicles required for the investment either exempt from customs duty or subject to a reduced rate and exempted from taxes in accordance with a Directive issued by the Ministry;

፳፩/ "**ቀረጥ"** በጉምሩክ አዋጅ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፤

21/ "**Duty**" shall have the meaning assigned under the Customs Proclamation;

፳፪/ **"ታክስ"** ማለት ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ወይም በአገር ውስጥ በሚመረቱ ዕቃዎች ላይ የሚሰበሰብ የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው፤

22/ "**Tax**" means Value Added Tax collected on goods imported into the country or produced domestically;

፳፫/ **"የጉምሩክ አዋጅ"** ማለት የጉምሩክ አዋጅ (እንደተሻሻለው) ቁጥር ፰፻፶፱/፪ሺ፮ ነው፤

23/ "**Customs Proclamation**" means Customs Proclamation (as amended) No. 859/2014;

፳፬/ **"ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር"** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የገንዘብ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

24/ "**Ministry**" **or** "**Minister**" means the Ministry of Finance, or Minister respectively;

፳፭/ በዚህ ደንብ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሁሉ የሴት ጾታን ይጨምራል፤

፳፮/ በአዋጁ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት እና ሐረጎች በዚህ ደንብ በተለየ ሁኔታ ትርጉም ካልተሰጣቸው በስተቀር ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፫. የተፈፃሚነት ወሰን

፩/ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ማበረታቻ በሚያስገኙ የኢንቨስትመንት መስኮች የሚሰማራ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት በሚሰጡ ማበረታቻዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፪/ በዚህ ደንብ ክፍል ሦስት የተደነገገውን ሳይጨምር የዚህ ደንብ ሌሎች ድንጋጌዎች በማዕድን፣ በነዳጅ፣ ወይም በተፈጥሮ ጋዝ ኢንቨስትመንት ላይም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

፬. አላማዎች

በዚህ ደንብ መሰረት የሚፈቀዱ የታክስ ማበረታቻዎች፤ በእነዚህ ሳይወሰን ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የማበረታታት አላማ ይኖራቸዋል፡-

፩/ የግብርና ኢንቨስትመንትን፤
፪/ አምራች ኢንቨስትመንትን፤
፫/ ገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካትን፤
፬/ የቴክኖሎጂ ሽግግርን፤
፭/ የስራ ፈጠራን፤
፮/ የአካባቢ ደህንነት ጥበቃን፤
፯/ የማዕድን እና ኢነርጂን፤

25/ Any term expressed in male gender in this Regulation shall be construed to include the female gender;

26/ Unless a different meaning is provided in this Regulation, words and phrases used in this Regulation shall have the meaning assigned to them in the Proclamation.

3. Scope of Application

1/ The provisions of this Regulation shall apply to incentives granted to encourage investment in sectors eligible for incentives.

2/ Without prejudice to the provisions of Part Three of this Regulation, other provisions of this Regulation shall also be applicable to mining, petroleum, or natural gas investment.

4. Objectives

Tax incentives allowed under this Regulation shall have one or more of the following incentive objectives, without being limited to these:

1/ Agricultural Investments;
2/ Manufacturing investment;
3/ Import substitution through domestic production;
4/ Technology transfer;
5/ Entrepreneurship;
6/ Protect the Environment;
7/ Mining and Energy;

፰/ የሀገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት በውጤታማ እና በብቃት መልማትን፤

፱/ የአገልግሎት ዘርፍን ፤

፲/ ተገቢ የሥራ ዕድል መፍጠርን፣ እና

፲፩/ የክልሎችን የተመጣጠነ እድገት፡፡

፭. መርሆዎች

ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት የሚሰጥ የታክስ ማበረታቻ የሚከተሉትን መርሆዎች በአንድነት የተከተለ መሆን አለበት፡-

፩/ በህግ ላይ የተመሰረተ፤ ግልጽ፤ በጊዜ የተገደበ፤

፪/ የመንግስትን የፋይናንስ አቅም መሰረት ያደረገ፤

፫/ በሕግ ይፋ በተደረገ መስፈርት መሰረት ያለአድልዎ የሚሰጥ፤

፬/ የታቀደውን ውጤት ያስገኘ መሆኑ ክትትል የሚደረግበት፤ እና

፭/ ህግ ተጥሶ በሚገኝበት ጊዜ የሚሰረዝና ተጠያቂነትን የሚያስከትል፡፡

8/ Ensure efficient and effective utilization of natural resources;

9/ Service sector;

10/ Create appropriate employment opportunities; and

11/ Balanced regional development.

5. Principles

Tax incentives designed to encourage investment shall be based on the following cumulative principles:

1/ Legally grounded, transparent, and time-bound;

2/ Based on the fiscal capacity of the Government;

3/ Granted without discrimination, based on legally established criteria;

4/ Subject to monitoring to ensure achievement of intended outcomes; and

5/ Revocable and enforceable with liability in the event of legal violations.

ክፍል ሁለት

የተፈቀዱ ማበረታቻዎች እና ቅድመ-ሁኔታዎች

፮. የተፈቀዱ ማበረታቻዎች

በዚህ ደንብ በተደነገገው መሰረት የሚከተሉት የማበረታቻ አይነቶች ሊፈቀዱ ይችላሉ፡-

፩/ የኢንቨስትመንት የካፒታል አላዋንስ፤

፪/ ከመደበኛው ያነሰ የገቢ ግብር፤

፫/ ከአማራጭ አነስተኛ ግብር ነፃ የመሆን፤

፬/ በትርፍ ድርሻ ላይ ከሚከፈል ግብር ነፃ የመሆን፤

፭/ ከካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ግብር ላይ ነፃ የመሆን፤

፮/ የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ማበረታቻ፡፡

፯. ማበረታቻ የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች

፩/ በዚህ ደንብ የተመለከቱት ማበረታቻዎች የሚሰጡት በሚከተሉት ሁኔታዎች ይሆናል፡-

ሀ/ ተጨማሪ አቅም ወይም እሴት ለሚፈጥሩ ኢንቨስትመንቶች፤

ለ/ አመልካቹ በታክስ ከፋይነት የተመዘገበ፤ ተፈላጊ ሁኔታዎችን የሚያሟላ እና ለእያንዳንዳንዱ ማበረታቻ ለሚሰጠው ፕሮጀክት ወይም የስራ ዘርፍ የተለየ የሂሳብ መዝገብ የሚያቀርብ ሲሆን፤

PART TWO

PERMITTED INCENTIVES AND PRE -CONDITIONS

6. Permitted Incentives

The following types of incentives may be granted pursuant to this Regulation:

1/ Investment capital allowance;

2/ Income tax at a reduced rate than the regular;

3/ Exemption from Minimum Alternative Tax;

4/ Exemption from dividend tax;

5/ Exemption from capital gains tax; and

6/ Customs duty and tax incentives.

7. Conditions for Granting Incentives

1/ The incentives provided under this Regulation shall be granted subject to the following conditions:

a) Investments that create additional production capacity or generate value addition;

b) The applicant is registered as a taxpayer, satisfies the prescribed requirements, and maintains separate accounting records for each investment project or line of business for which the incentive is granted;

ሐ/ ማበረታቻዎቹ ለተቋቋሙለት ገቢ እና ለተፈቀዱት ወጪዎች ብቻ የሚውሉ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚያስችል አኳኋን የታጠረ ስርአት በመዘርጋት፤

መ/ በዚህ ደንብ በተፈቀደው መሰረት ካልሆነ በስተቀር ለተወሰነ ጊዜ እና ለሌላ ወገን ማስተላለፍ በማያስችል አኳኋን፣ እና

ሠ) በዚህ ደንብ እና ደንቡን ተከትሎ ከሚወጡ መመሪያዎች በስተቀር ተደራራቢ ማበረታቻ እንዳይኖር በሚያስችል ሁኔታ፡፡

ፀ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶችን ሳይጨምር በዚህ ደንብ የተመለከተው መሰረት ከመደበኛው ያነሰ የገቢ ግብር ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉት ቢያንስ ፲ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (አስር ሚሊዮን) የአሜሪካን ዶላር ወይም ተመጣጣኙን በኢትዮጵያ ብር ስራ ላይ የሚያውሉ ባለሃብቶች ናቸው።

፰/ አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች በዚህ ደንብ የተመለከተው ማበረታቻ ተጠቃሚ የሚሆኑት ሚኒስቴሩ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመመካከር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

c) with a system of ring fencing established to ensure that the incentives are utilized exclusively for the purposes for which they are intended and for eligible expenditure ;

d) except as expressly permitted under this Regulation for a limited period and in a manner that does not allow transfer to any other party; and

e) except as explicitly authorized under this Regulation or Directives issued hereunder in a manner that does not allow multiple incentives.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, and excluding small and medium enterprises, investors shall be eligible for a reduced income tax rate as provided under this Regulation only if they invest at least USD 10,000,000 (ten million United States Dollars) or its equivalent in Ethiopian Birr.

3/ Small and medium enterprises shall be beneficiaries of the incentives provided under this Regulation in accordance with Directives to be issued by the Ministry in consultation with relevant government organs.

፬/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም **"አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች"** ማለት የስራ እድል በመፍጠር እና ገቢ በማመንጨት ላይ የሚገኙ በቴክኖሎጂ፣ በኮንስትራክሽን፣ በማምረት እና አገልግሎት በመስጠት ስራ ላይ የተሰማሩ እና ፈጠራን እና የኢኮኖሚ ለውጥን ሊያመጡ የሚችሉ በስራ እና ክህሎት ሚኒስቴር እና ሌሎች ሥልጣን በተሰጣቸው የመንግሥት አካላት እውቅና የተሰጣቸው ድርጅቶች ናቸው።

ክፍል ሶስት
የገቢ ግብር ማበረታቻ

፰. ለልዩ የኢኮኖሚ ዞን አልሚ እና ንዑስ አልሚ የሚሰጥ የገቢ ግብር ማበረታቻ

፩/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ እና ንዑስ አልሚ፡-

ሀ) ግብር ከሚከፈልበት አመታዊ ገቢያቸው ላይ ለ፲ (አስር) አመታት ከመደበኛው ያነሰ የ፭ ፐርሰንት (አምስት በመቶ) የገቢ ግብር ማስከፈያ መጣኔ ተፈጻሚ ይደረግላቸዋል። ሆኖም ከዚያ በኋላ ባሉት አመታት በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሰረት የንግድ ትርፍ ግብር ይከፍላሉ፤

ለ) ለባለአክሲዮኖች በሚከፍሉት የትርፍ ድርሻ ላይ ከሚከፈል ታክስ ለ፭ (አምስት) አመታት ነጻ ይሆናሉ፤

4/ For the purposes of this Article, **"small and medium enterprises"** means enterprises engaged in technology, construction, manufactu ring, and service sectors that create job opportunities and generate income, and which are capable of fostering innovation and economic transformation, and are recognized as such by the Ministry of Labor and Skills and other Authorized Government organs.

PART THREE
INCOME TAX INCENTIVE

8. Income Tax Incentive for Special Economic Zone Developers and Sub-Developers

1/ A Special Economic Zone Developer or Sub-Developer ፡

a) reduced income tax rate of 5% (five percent) shall apply to annual taxable income for a period of 10 (ten) years commencing from the date of issuance of a business license. Thereafter, the standard business income tax rate under the Income Tax Proclamation shall apply;

b) They shall be exempt from tax on dividends distributed to shareholders for a period of 5 (five) years;

ሐ) ከአማራጭ አነስተኛ ግብር ለ፲ (አስር) አመታት ነጻ ይሆናሉ።

፪/ በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩት ማበረታቻዎች ተጠቃሚ ለመሆን የሚችለው በልዩ የኢኮኖሚ ዞን አዋጅ መሰረት በኢንቨስትመንት ቦርድ እውቅና የተሰጠው ልዩ የኢኮኖሚ ዞን አልሚ እና ንዑስ አልሚ ይሆናል።

፫/ ከመሀል አገር ርቀው ለተቋቋሙ ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች አልሚዎች እና ንዑስ አልሚዎች የሚፈቀደው የገቢ ግብር ማበረታቻ ጊዜ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፱. ለልዩ የኢኮኖሚ ዞን ድርጅት የሚሰጥ የገቢ ግብር ማበረታቻ

፩/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት በሰንጠረዥ ፩ በተጠቀሰው መሰረት ከመደበኛው ያነሰ የ፲፭ ፐርሰንት (አስራ አምስት በመቶ) የገቢ ግብር ማስከፈያ መጣኔ ተፈጻሚ ይደረግላቸዋል። ሆኖም ከዚያ በኋላ ባሉት አመታት በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሰረት የንግድ ትርፍ ግብር ይከፍላሉ።

c) They shall be exempt from the Minimum Alternative Tax for a period of 10 (ten) years.

2/ The eligible investor entitled to the incentives provided under this Article shall be a Developer or Sub-Developer of a Special Economic Zone recognized as such by the Investment Board pursuant to the Special Economic Zone Proclamation.

3/ The Ministry shall determine by a Directive the income tax incentive period granted to Special Economic Zones Developers and Sub-Developers established far from central regions.

9. Income Tax Incentives for Special Economic Zone Enterprises

1/ Special Economic Zone Enterprises shall be subject to a reduced income tax rate of 15% (fifteen percent) as specified in Table 1; thereafter, the standard business income tax rate under the Income Tax Proclamation shall apply.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም ማዳበሪያ በማምረት ስራ ላይ የተሰማራ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት ግብር ከሚከፈልበት አመታዊ ገቢው ላይ ለ፲ (አስር) አመታት ከመደበኛው ያነሰ ፭ ፐርሰንት (አምስት በመቶ) የገቢ ግብር ማስከፈያ መጣኔ ተፈጻሚ ይደረግለታል። ሆኖም ከዚያ በኋላ ባሉት አመታት በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሰረት የንግድ ትርፍ ግብር ይከፍላል።

፫/ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን የገቢ ግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ፩ ከተዘረዘሩት የስራ መስኮች በአንዱ የተሰማራ ሲሆን ነው።

፬/ ከመሀል አገር ርቀው ለተቋቋሙ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ድርጅቶች የሚፈቀደው የገቢ ግብር ማበረታቻ ጊዜ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፭/ በዚህ ደንብ ሰንጠረዥ ፩ በተመለከቱ የስራ ዘርፎች ውስጥ የሚካተቱትን ንዑስ የስራ መስኮች የሚዘረዝርና ለዋናው ዘርፍ የተቀመጠውን የጊዜ ገደብ ሳይበልጥ ለንዑስ ዘርፎች ተፈፃሚ የሚሆነውን የገቢ ግብር ማበረታቻ የቆይታ ጊዜ የሚወስን መመሪያ ሚኒስቴሩ ያወጣል፡፡

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article an enterprise engaged in the manufacturing of fertilizer in a Special Economic Zone shall pay a reduced rate of 5% (five percent) on its annual taxable income for 10 (ten) years from the date of commencement of operations; thereafter, the standard business income tax rate under the Income Tax Proclamation shall apply.

3/ A Special Economic Zone Enterprise shall be eligible for the income tax incentive provided under Sub-Article (1) of this Article only if it is engaged in one of the sectors listed in Table 1 annexed to this Regulation.

4/ The Ministry shall determine by a Directive the income tax incentive period granted to special economic zones enterprises established far from Central Regions.

5/ The Ministry shall issue a Directive specifying the sub-sectors included under each sector listed in Table 1 and determine the duration of the applicable income tax incentive for each sub-sector, provided that such duration shall not exceed the time limit prescribed for the principal sector.

፲. ለስታርታፕ የሚሰጥ የገቢ ግብር ማበረታቻ

አግባብነት ባለው ሕግ ስያሜ የተሰጠው ማናቸውም ስታርታፕ፡-

፩/ ስራ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ለሚቆጠር የ፲ አመት (አስር አመት) ጊዜ ግብር በሚከፈልበት ገቢው ላይ ከመደበኛው ያነሰ ፭ፐርሰንት (አምስት በመቶ) የገቢ ግብር ማስከፈያ መጣኔ ተፈጻሚ ይደረግለታል። ከተጠቀሰው ጊዜ በኋላ በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሰረት የንግድ ትርፍ ግብር ይከፍላል፤

፪/ ለባለአክሲዮኖች ከሚከፍለው የትርፍ ድርሻ ላይ ከሚከፈል ታክስ ለ ፭ (አምስት) አመታት ነጻ ይሆናል።

፲፩. ለስታርታፕ ምህዳር ገንቢ የሚሰጥ ማበረታቻ

አግባብነት ባለው ሕግ እውቅና የተሰጠው የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ፤

፩/ በስታርታፕ ውስጥ ያለውን የባለቤትነት ድርሻ በመሸጥ የሚያገኘው የካፒታል ዋጋ እድገት ጥቅም ግብር አይከፈልበትም፤

፪/ ከስታርታፕ በሚቀበለው የትርፍ ድርሻ ላይ ከሚከፈል ታክስ ለ ፭ (አምስት) አመታት ነጻ ይሆናል፤

10. Income Tax Incentives for Startups

A startup recognized in accordance with the relevant law:

1/ A reduced income tax rate of 5% (five percent) shall apply to its taxable income for a period of 10 (ten) years from the date of commencement of business; thereafter, the standard business income tax rate shall apply;

2/ Exemption from tax on dividends distributed to shareholders for a period of 5 (five) years.

11. Incentives for Startup Ecosystem Builders

A startup ecosystem developer recognized under the relevant law ;

1/ Capital gains realized from the sale of ownership interests in a startup shall be exempt from tax፡

2/ Dividends received from a startup shall be exempt from tax for a period of five (5) years;

፫/ በስታርታፕ ውስጥ ኢንቨስት ያደረገ ባለሀብት በስታርታፕ ውስጥ ባዋለው ሃብት ላይ ኪሳራ የደረሰበት መሆኑን ማሳየት እስከቻለ ድረስ በስታርታፑ ውስጥ ለደረሰበት የኪሳራ መጠን ልክ ብቻ ከአማራጭ አነስተኛ ግብር ለ ፫ (ሦስት) አመታት ነጻ ይሆናል።

3/ An investor who has invested in a start-up shall be exempt from Minimum Alternative Tax for a period of 3 (three) years, but only to the extent of the loss incurred in the start-up, provided the investor can demonstrate that they suffered a loss due to their investment in the start-up.

፲፪. ለከባቢ አየር ደህንነት ጥበቃ የሚሰጥ ማበረታቻ

12. Incentives for Environmental Protection

፩/ በካርቦን ልውውጥ ገበያ ወይም በበካይ ጋዝ አመንጪ የገበያ ስርአት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ እና አግባብ ባለው የመንግስት አካል እውቅና የተሰጣቸው ኩባንያዎች ስራ ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ለ ፲ (አስር) አመታት ግብር በሚከፈልበት ገቢያቸው ላይ ከመደበኛው ያነሰ ፲፭ ፐርሰንት (አስራ አምስት በመቶ) የንግድ ትርፍ ግብር ይከፍላሉ።

1/ Companies participating in the carbon trading market or the emissions trading system and recognized by the Environmental Protection Authority shall be subject to a reduced business income tax rate of 15% (fifteen percent) on taxable income for a period of 10 (ten) years from the date of commencement of operations.

፪/ ታዳሽ ያልሆነ ሃይል ሲጠቀም የነበረ ባለሀብት በምርት ወይም በአሰራር ሂደቱ ቢያንስ ፶ ፐርሰንት (ሃምሳ በመቶ) በራሱ ያመነጨውን ታዳሽ ኃይል የሚጠቀም ከሆነ በዚህ አንቀጽ በተመለከተው መጠን በታዳሽ ሃይል መጠቀም ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ላሉት ተከታታይ ፭ (አምስት) ዓመታት ብቻ ግብር በሚከፈልበት ገቢው ላይ ከመደበኛው ያነሰ ፲፭ ፐርሰንት (አስራ አምስት በመቶ) የንግድ ትርፍ ግብር ይከፍላል።

2/ Any investor who utilizes at least 50% (fifty percent) renewable energy generated by himself in his production or operations, having previously used non-renewable energy, shall be subject to a reduced business income tax rate of 15% (fifteen percent) on taxable income for 5 (five) consecutive years from the date of commencement of renewable energy usage.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው ማበረታቻ ለምርት ተግባር ከሚጠቀምባቸው ግብአቶች መካከል ፶ ፐርሰንት (ሃምሳ በመቶ) እና ከዚያ በላይ የሆኑትን በአገር ውስጥ የሚገኙ ውዳቂ ቁሳቁሶችን መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል የሚያመርት መሆኑ አግባብነት ባለው ባለስልጣን ለተረጋገጠ ባለሀብትም ተፈጻሚ ይሆናል።

፬/ ባለሃብቱ ለማበረታቻው ብቁ ለመሆን አግባብ ባለው የመንግስት አካል የተረጋገጠ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተውን የታዳሽ ኃይል አጠቃቀም መጠን ማሟላቱን የሚያሳይ ዓመታዊ የኃይል ኦዲት ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

፭/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃጸም ሚኒስቴሩ ዝርዝር መመሪያን ያወጣል፡፡

፲፫. ከልዩ የኢኮኖሚ ዞን ውጪ የተሰማሩ ባለሀብቶች የገቢ ግብር ማበረታቻ

፩/ ከልዩ የኢኮኖሚ ዞን ውጪ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ፩ በተዘረዘሩ የስራ መስኮች ላይ የተሰማራ ባለሃብት በሰንጠረዡ በተመለከተው መሰረት ከመደበኛው ያነሰ የ፲፭ ፐርሰንት (አስራ አምስት በመቶ) የገቢ ግብር ማስከፈያ መጣኔ ተፈጻሚ ይደረግለታል። ሆኖም ከዚያ በኋላ ባሉት አመታት በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሰረት የንግድ ትርፍ ግብር ይከፍላሉ።

3/ The incentive provided under Sub-Article (2) of this Article shall also apply to an investor who obtains certification from the competent authority confirming that 50% (fifty percent) or more of the production inputs utilized are derived from the recycling of recycled materials sourced locally.

4/ To qualify for the incentive under Sub-Article (2), the investor shall submit an annual energy audit report certified by the competent authority, demonstrating compliance with the renewable energy usage requirement.

5/ The Ministry shall issue a detailed Directive for the implementation of this Article.

13. Income Tax Incentives for Investors Engaged Outside the Special Economic Zone

1/ An investor operating outside a Special Economic Zone and engaged in activities listed in Table 1 annexed to this Regulation shall be subject to a lower income tax rate of 15% (fifteen percent) as specified in the Schedule. However, in the subsequent years, they shall pay business profit tax in accordance with the provisions of the Income Tax Proclamation.

፪/ ሚኒስቴሩ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ፩ በተመለከቱ የስራ መስኮች ውስጥ የሚካተቱትን ንዑስ የስራ መስኮችን የሚዘረዝር፣ ተጨማሪ የስራ መስኮችን በሰንጠረዡ ውስጥ ለማካተት የሚያስችል እንዲሁም ለንዑስ ዘርፎች ተፈፃሚ የሚሆነውን የገቢ ግብር ማበረታቻ ቆይታ ጊዜን የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡

፫/ ከመሀል አገር ርቀው ከልዩ የኢኮኖሚ ዞን ውጭ ለተቋቋሙ ባለሀብቶች የሚፈቀደው የገቢ ግብር ማበረታቻ የጊዜ ርዝመት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፲፬. የካፒታል ወጪ ተቀናሽ

፩/ ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በሆነው ሰንጠረዥ ፪ ለተዘረዘሩ የኢንቨስትመንት መስኮች ለዋሉ የካፒታል እና የግንባታ እቃዎች ለወጣ ተቀባይነት ያለው ወጪ በሰንጠረዡ መሰረት የካፒታል ወጪ ተቀናሽ ይፈቀዳል።

፪/ የካፒታል ወጪ ተቀናሽ ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉት ቢያንስ ፪ ሚሊዮን (ሁለት ሚሊዮን) የአሜሪካን ዶላር ወይም ተመጣጣኙን የኢትዮጵያ ብር በኢንቨስትመንት ስራ ላይ ያዋሉ ባለሀብቶች ብቻ ናቸው።

2/ The Ministry shall issue a Directive listing the sub-sectors included under the fields of activity specified in Table 1 attached to this Regulation, enabling the inclusion of additional fields of activity into the Table, and determining the duration of the income tax incentive applicable to the sub-sectors.

3/ The Ministry shall determine by a Directive the income tax incentive period granted to investors established outside of special economic zones and far from Central Regions.

14. Deductible Capital Expenditure

1/ Deductible capital expenditure shall be granted for eligible expenditure on capital goods and building materials utilized in the investment areas listed in Table 2 annexed to this Regulation.

2/ Only investors who invest at least Two million United States Dollars (USD 2,000,000) or its equivalent in Birr in investment activities shall qualify for the deductible capital expenditure.

፫/ የካፒታል ወጪ ተቀናሽ የሚፈቀደው በሚከተለው ሁኔታ ይሆናል፡-

ሀ) የካፒታል እቃው በግብር ከፋዩ ባለቤትነት ስም ያለ ከሆነ፤

ለ) የካፒታል ዕቃው ሙሉ በሙሉ እና በብቸኝነት ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለማግኘት የዋለ ከሆነ ወይም ሙሉ በሙሉ ወይም በብቸኝነት ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለማግኘት ያልዋለ ከሆነ፣ ታክስ ለሚከፈልበት ገቢ የዋለውን መጠን በትክክል ለይቶ በማስላት በዚያው መጠን ብቻ፤

ሐ) ለመደበኛ ወጪ ሳይሆን በትክክል ለካፒታል ወጪ በዋለው መጠን ብቻ፤

መ) የካፒታል ዕቃው ከተፈራበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን ወይም ያለአገልግሎት በተቀመጠበት ጊዜ ጭምር ሳይሆን፣ ገቢ በሚያመነጭበት ጊዜ ብቻ፤ እና

ሠ) ግብር ከፋዩ ትክክለኛ የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ ከሆነ፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም ለካፒታል ዕቃዎች ኪራይ የሚሰጠው የካፒታል ወጪ ተቀናሽ ለተከፈለው መጠን ብቻ ይሆናል፡፡

3/ Deductible capital expenditure shall be granted under the following conditions:

a) The capital goods are owned by the taxpayer;

b) The capital goods are used wholly and exclusively for the purpose of generating taxable income; or where not wholly or exclusively used, by identifying and assessing the portion used for generating taxable income;

c) The capital expenditure utilized for capital goods and not for recurrent operating expenditure;

d) The allowance shall apply from the period in which the capital goods are placed into use for income-generating purposes, not from the date of purchase or when idle; and

e) The taxpayer maintains accurate and reliable accounting records.

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (3) (a) of this Article, the deductible capital expenditure granted in respect of leased capital goods shall be limited to the actual lease payments made.

ሸ/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "ተቀባይነት ያለው ወጪ" ማለት ለካፒታል እና ለግንባታ ዕቃዎች ማፍሪያ የዋለ እና ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ወጪ ነው።

፲፭. ለሳይንሳዊ ምርምር የሚሰጥ ማበረታቻ

፩/ ማናቸውም ባለሀብት በንግድ ስራው ገቢ ውስጥ የተካተተውን ገቢ ለማግኘት በአንድ የግብር አመት ውስጥ ከንግድ ስራው እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ በራሱ ወይም በሶስተኛ ወገን አማካኝነት ለሚያከናውነው ሳይንሳዊ ምርምር የሚያወጣው ወጪ ተቀናሽ ይደረጋል።

፪/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም፡-

ሀ) "ሳይንሳዊ ምርምር" ማለት የሰውን ልጅ እውቀት ለማሻሻል በተፈጥሮ ወይም ተግባራዊ ሳይንስ ረገድ የሚከናወን ማናቸውም እንቅስቃሴ ነው፤

ለ) "የሳይንሳዊ ምርምር ወጪ" ማለት የንግድ ስራ የሚያካሂድን ሰው በሚመለከት በውስጥ አቅም ለሚከናወን ሳይንሳዊ ምርምር የሚወጣ ወጪ ወይም የንግድ ስራውን ለማሳደግ ለሚጠቀምበት የሳይንሳዊ ምርምር ተቋም የንግድ ስራውን ለማሳደግ ለሚደረግ ሳይንሳዊ ምርምር የሚያደርገውን መዋጮ የሚጨምር ሲሆን የሚከተሉትን አያካትትም፡-

5/ For the purpose of this Article "**Eligible Expenditure**" means expenditure on capital goods or construction that meets the criteria prescribed in a Directive issued by the Ministry.

15. Incentives for Scientific Research

1/ Any investor who incurs expenditure for scientific research conducted internally or through a third party in connection with its business activities during a tax year shall be allowed for deduction of expenditures made for such scientific research.

2/ For the purpose of this Article:

a) "**Scientific Research**" means any activity undertaken in the natural or applied sciences aimed at advancing Human Being knowledge;

b) "**Scientific Research Expenditure**" means expenditures made for scientific research by a person engaged in business activities within the institution or contributions made to a another scientific research institution for the purpose of advancement of its business, but does not include the following:

1) የእርጅና ቅናሽ ለሚደረግለት ንብረት ወይም ግዙፋዊ ሃልዎት ለሌለው ንብረት የሚወጣ ወጪ፤
2) ለመሬት ወይም ለህንጻ የሚወጣ ወጪ፤እና
3) የተፈጥሮ ሃብት ስለመኖሩ፣ ያለበትን ቦታ፣ ብዛት ወይም ጥራቱን ለማወቅ የሚወጣ ወጪ።

ሐ) **"የሳይንሳዊ ምርምር ተቋም"** ማለት የሳይንሳዊ ምርምር ለማድረግ የተቋቋመ ማህበር ፣ ኢንስቲትዩት ወይም ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ነው።

፲፮. <u>በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በመመዝገብ የሚሰጥ ማበረታቻ</u>

፩/ አክሲዮኖቹን በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ፈቃድ በተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ በይፋ በማስመዝገብ ለግብይት ያቀረበ ማንኛውም ኩባንያ አክሲዮኖቹ በገበያው ላይ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ለ፫ (ሦስት) ዓመታት ከመደበኛው ያነሰ ፳፭ ፐርሰንት (ሃያ አምስት በመቶ) የንግድ ትርፍ ግብር ይከፍላል።

i) Expenditures made on depreciable assets or intangible assets;

ii) Expenditures made on land or buildings; and

iii) Expenditure relating to the existence, location, quantity, or quality of natural resources.

c) **"Scientific Research Institution"** means an association, institute, or higher education institution established to conduct scientific research.

16. <u>Incentives for Listing in the Securities Market</u>

1/ Any company that publicly lists its shares in a securities exchange licensed by the Ethiopian Capital Market Authority and offers them for trading shall be subject to a reduced business income tax rate of twenty-five percent (25%) for a period of three (3) years from the date of initial public offering.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመላከተው ማበረታቻ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ አክሲዮኖቻቸውን ለግብይት ያቀረቡ ኩባንያዎች እና የፋይናንስ ተቋማት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰጠው መብት ተፈጻሚ የሚሆነው ኩባንያው በማበረታቻ ጊዜው ውስጥ በገበያው መዝገብ ላይ ከቀጠለ እና በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን እንዲሁም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተጣሉትን ሁሉንም ግዴታዎችን አሟልቶ ሲገኝ ብቻ ነው ይህ ካልሆነ ማበረታቻው መስፈርቶቹን ባላሟላበት ወይም ከምዝገባ በተሰረዘበት የግብር ዓመት ወዲያውኑ ይቋረጣል።

፲፯. በገቢ ግብር ማበረታቻ ዘመን ገቢን ስለማሳወቅ

፩/ ማንኛውም ባለሀብት በዚህ ደንብ የተመለከቱት የገቢ ግብር ማበረታቻዎች ተጠቃሚ የሚሆነው በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሂሳብ መዝገቡን አግባብ ላለው የታክስ ባለስልጣን ሲያቀርብ ይሆናል፡፡

፪/ ማንኛውም ባለሀብት የገቢ ግብር ማበረታቻ የሚያስገኙ ሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ የኢንቨስትመንት መስኮች ላይ የተሰማራ እንደሆነ ለታክስ ማበረታቻ ዓላማ የእያንዳንዱን ኢንቨስትመንት ገቢ ለየብቻ ማሳወቅ አለበት፡፡

2/ The incentive referred to in Sub Article (1) of this Article shall not be applicable to companies that have offered their shares for trading on an over the counter market and to financial institutions.

3/ Eligibility under Sub Article (1) shall apply only if the company remains continuously registered in the securities exchange and complies with all obligations imposed by the Ethiopian Capital Market Authority and other applicable laws during the incentive period. Non-compliance shall result in immediate termination of the incentive in the fiscal year in which the violation occurs.

17. Reporting Income During the Tax Incentive Period

1/ An investor shall be entitled to the income tax incentives under this Regulation upon submission of accounting records to the appropriate Tax Authority, in accordance with the Income Tax Proclamation.

2/ Any investor engaged in two or more investment fields that are eligible for income tax incentives shall report the income of each investment separately for tax incentive purposes.

፫/ የገቢ ግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆነ ባለሀብት፡-

ሀ) በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሂሳብ መዝገቡን ያላቀረበ እንደሆነ ግዴታውን ላልተወጣበት የግብር ዘመን የግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ መሆኑ ቀሪ ይሆናል፤

ለ) የሂሳብ መዝገቡን በህግ ከተደነገገው ጊዜ ዘግይቶ ካቀረበ በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሰረት አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል።

፬/ ባለሀብቱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገውን ግዴታው ያልተወጣው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በተመለከተ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፫ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፲፰. የገቢ ግብር ማበረታቻ ስለሚጀምርበት ጊዜ

፩/ የገቢ ግብር ማበረታቻ መቆጠር የሚጀምረው ባለሀብቱ የንግድ ሥራ ፈቃድ ከወሰደበት ቀን አንስቶ ይሆናል፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈፃፀም ባለሀብቱ አግባብ ያለው መስሪያ ቤት የሰጠውን የንግድ ሥራ ፈቃድ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት፡፡

3/ An investor benefiting from an income tax incentive:

a) Failure to submit accounting records as required under the Income Tax Proclamation shall invalidate the incentive for the applicable tax period;

b) If accounting records are submitted after the prescribed deadline, administrative penalties shall apply in accordance with the Tax Administration Proclamation.

4/ Where as provided in a Directive issued by the Minister the investor fails to fulfill its obligations as stipulated in Sub Article 1 of this Article due to circumstances beyond its control, Sub Article 3 of this Article shall not apply.

18. Commencement of Income Tax Incentives Period

1/ The period of income tax incentives under this Regulation shall commence on the date the investor obtains a business license.

2/ For the implementation of Sub Article (1) of this article, the investor shall submit the business license issued by the competent authority to the investment institution.

፫/ ማንኛውም ባለሀብት ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት ጀምሮ ግብር የከፈለ እንደሆነና ከዚህ በኋላ የገቢ ግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ መሆኑን የሚገልፅ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከሆነ የከፈለውን ግብር ተመላሽ መጠየቅ አይችልም፡፡

፬/ ባለሃብቱ የገቢ ግብር ማበረታቻ ጥያቄውን ያቀረበው ማበረታቻው የሚቆጠርበት ቀን ካለፈ በኋላ ዘግይቶ ከሆነ ተጠቃሚ የሚሆነው ለቀሪው የማበረታቻ ጊዜ ብቻ ይሆናል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በሚዘረዘሩ ልዩ ሁኔታዎች የገቢ ግብር ማበረታቻ መቆጠር የሚጀምርበትን የተለየ ጊዜ ሊወስን ይችላል።

፲፱. ተጠቃሚነት ላይ ስለሚጣል ገደብ

፩/ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚያስገኝ ኢንቨስትመንት ባለቤት የሆነ ሰው በቂ ባልሆነ ምክንያት ወይም ተጨማሪ ማበረታቻ ለማግኘት በማቀድ የተሠማራበትን ኢንቨስትመንት ዘግቶ መልሶ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ በሚያሰጥ ኢንቨስትመንት ላይ ከተሰማራ ቢያንስ በዘጋው ኢንቨስትመንት የተጠቀመበትን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለሚያክል ጊዜ የገቢ ግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ አይሆንም፡፡

3/ An investor shall not be entitled to refund of the tax paid if the tax incentive certificate is issued after taxes have been paid on the production or rendition of services carried out before such date.

4/ If the investor submits the income tax incentive request after the date on which the incentive is to take effect the investor shall only be eligible for the unused remainder of the incentive period.

5/ Notwithstanding Sub Article (1) of this Article, the Ministry may issue a Directive establishing an alternative commencement date of the income tax incentives for special circumstances.

19. Limitation on Entitlement

1/ Where an investor eligible for incentives closes an investment without reasonable cause or for the purpose of securing additional incentives and subsequently engages in another incentive-eligible investment, the investor shall not be entitled to an income tax incentive for a period at least equivalent to the period for which incentives were previously enjoyed.

፪/ ሚኒስቴሩ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም የሚያግዝ መመሪያ ያወጣል።

፳. <u>ተደራራቢ የገቢ ግብር ማበረታቻ</u>

በዚህ ደንብ መሰረት ባለሀብቱ ከአንድ ጊዜ በላይ ከመደበኛው ያነሰ የገቢ ግብር ማስከፈያ መጣኔ የገቢ ግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ የመሆን መብት የሚኖረው ከሆነ የተሻለ ማበረታቻ የሚያስገኘውን አንዱን ማበረታቻ ብቻ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

<u>ክፍል አራት</u>

<u>የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ማበረታቻ</u>

፳፩. <u>ለልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ፣ ንዑስ አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት ስለሚሰጥ የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ማበረታቻ</u>

፩/ በልዩ የኢኮኖሚ ዞን አዋጅ መሰረት እውቅና በተሰጠው ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ውስጥ በስራ ላይ የተሰማራ አልሚ፣ ንዑስ አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት ወደ አገር የሚያስገቧቸው የካፒታል እና የግንባታ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆነው ወደ አገር ሊገቡ ይችላሉ፡፡

2/ The Ministry shall issue directives to support the implementation of Sub-Article (1) of this Article.

20. <u>Overlapping Income Tax Incentive</u>

Where an investor is eligible for more than one reduced rate income tax incentive under this Regulation, the investor shall only benefit from the incentive providing the greater advantage.

<u>PART FOUR</u>

<u>CUSTOMS DUTY AND TAX INCENTIVES</u>

21. <u>Customs Duty and Tax Incentives for Special Economic Zone Developers, Administrators or Enterprises</u>

1/ A Developer, Sub Developer, Administrator, or enterprise operating in a Special Economic Zone recognized under the Special Economic Zone Proclamation may import capital goods and construction equipment into the country benefiting from customs duty and tax incentives.

፪/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጠው አልሚ፣ ንዑስ አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት በራሱ፣ በስራ ተቋራጩ ወይም በተመዘገበ የሎጂስቲክስ ኦፕሬተሩ አማካኝነት ለኢንቨስትመንቱ አላማ እንዲውሉ የተገዙ የግንባታ ዕቃዎችን እና የካፒታል ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ በመሆን ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ማስገባት ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሰረት የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ፣ ንዑስ አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት ወደ አገር የሚያስገቧቸው ዕቃዎች የጊዜ እና የመጠን ገደብ ሳይደረግባቸው በማናቸውም ጊዜ ወደ አገር ሊገቡ ይችላሉ፡፡

፳፪. ከልዩ የኢኮኖሚ ዞን ውጪ ላሉ የሚሰጥ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ

፩/ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፫ (ሦስት) ከተዘረዘሩት የሥራ መስኮች በአንዱ የተሠማራ ባለሀብት ለሚያቋቁመው አዲስ ኢንቨስትመንት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ በመሆን የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎችን ወደ አገር ማስገባት ይችላል፡፡

2/ Developers, Administrators, or Enterprises that have been granted an investment license may import construction materials and capital goods purchased for their own investment directly, through their contracting agent, or via a registered logistics operator into the Special Economic Zone, benefiting from customs duty and tax incentives.

3/ Pursuant to Sub Articles (1) and (2) of this Article, Developers, Administrators, or Enterprises operating within the Special Economic Zone may import goods into the country without limitation as to quantity or timing.

22. Customs Duty and Tax Incentives Granted outside the Special Economic Zone

1/ An investor engaged in one of the fields of activity listed in Table 3 (Three) annexed to this Regulation may import capital goods and construction materials for a new investment by benefiting from customs duties and tax incentives.

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም ባለሀብቱ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ወደ አገር እንዲገቡ የሚፈልጋቸውን የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ዝርዝር ወይም እንደአግባብነቱ ዝርዝሮቹን የሚያስረዳ ሰነድ ግንባታው የሚጠይቀውን ግብዓቶች አይነትና መጠን የሚያሳይን የጸደቀ የተፈላጊ ዕቃ ብዛት ሰነድ አባሪ በማድረግ በሕግ ስልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብ ማስፈቀድ ይኖርበታል፡፡

3/ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆነ ባለሀብት ከአገር ውስጥ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ወይም ከአስመጪ የካፒታል ወይም የግንባታ ዕቃዎችን ሲገዛ ዕቃዎቹን ለማምረት በግብዓትነት በዋሉት ጥሬ ዕቃዎች ወይም ግብዓቶች ላይ የተከፈለው የጉምሩክ ቀረጥ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ባለሀብቱ የካፒታል እና የግንባታ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ወደ አገር ማስገባት የሚችለው የንግድ ፈቃድ እስከሚያወጣ ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ይሆናል፡፡

2/ For the implementation of Sub-Article (1) of this Article, the investor shall submit the list of capital goods and approved construction materials, as appropriate, to be imported with customs duty and tax incentive together with supporting documents such as a bill of quantities for construction materials for approval by the competent authority.

3/ Where an investor entitled to customs duty and tax incentives purchases capital goods or construction materials from local manufacturing industries, the investor shall be refunded the import duties and taxes paid on such raw materials or components used as inputs for the production of such goods.

4/ The investor may import capital goods and construction materials as a beneficiary of customs duty and tax incentives In accordance with Sub-Article (1) of this Article, only up to the date of issuance of the business license.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው ቢኖርም ኢንቨስትመንቱ በምዕራፍ የሚከናወን ሲሆን እና ለእያንዳንዱ ምዕራፍ የተለያዩ የካፒታል እና የግንባታ ዕቃዎችን በተለያዩ ጊዜያት ወደ አገር ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ሲሆን ይህም በባለሀብቱ የቢዝነስ ዕቅድ እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፮ መሰረት በሚፈረመው የአፈጻጸም ስምምነት ላይ የተመለከተ ከሆነ ባለሀብቱ የንግድ ፈቃድ ካወጣ በኋላ ለሚቀጥሉት ምዕራፎች የካፒታል እና የግንባታ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ በመሆን ሊያስገባ ይችላል፡፡

5/ Notwithstanding Sub-Article (4) of this Article, where an investment is implemented in phases and it is necessary to import different capital goods and construction materials at different times for each phase, as reflected in the investor's business plan and the implementation agreement concluded pursuant to Article 26 of this Regulation, the investor shall, following the issuance of a business license, be entitled to import capital goods and construction materials for subsequent phases as a beneficiary of customs duty and tax incentives.

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሰረት ተጠቃሚ ለመሆን ባለሀብቱ ጥያቄ ሲያቀርብ በጥያቄው መሰረት ከመፈቀዱ በፊት ለቀደመው ምዕራፍ በተፈቀደው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ መሰረት ወደ አገር ውስጥ ያስገባቸው ዕቃዎች ለታለመው ዓላማ የዋሉ ስለመሆኑ እና ባለሀብቱ የገባውን የአፈጻጸም ውል ያከበረ መሆኑ በተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ በቅድሚያ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

6/ When an investor requests to benefit from the incentives provided under Sub-Article (5) of this Article, it shall first be verified by the Regulatory Institutions whether the goods imported benefitting from the customs duty and tax incentives granted for the preceding phase were utilized for their intended purpose and whether the investor has complied with the implementation agreement concluded.

፯/ በዚህ አንቀፅ መሰረት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ የካፒታል እና የግንባታ ዕቃዎች ዝርዝር ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

7/ The list of capital goods and construction materials that may be imported with customs duty and tax incentives pursuant to this Article shall be determined by a Directive issued by the Ministry.

፳፫. ተሽከርካሪዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ስለመሆን

፩/ ሚኒስቴሩ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ዓይነትና ባህሪ መሠረት በማድረግ ለኢንቨስትመንት ዓላማ የሚውሉ የጭነት፣ የህዝብ ማመላለሻ እና ልዩ ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው እንዲገቡ ለኢንቨስትመንት ቦርድ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የቀረበው ሃሳብ በቦርዱ ተቀባይነት ሲያገኝ ሚኒስቴሩ ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ነፃ ሆነው ወደ አገር ውስጥ የሚገቡበትን ሁኔታ የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡

፳፬. በጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃን ስለማስተላለፍ

፩/ በጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ወደ አገር ውስጥ የገባ የካፒታል ዕቃ አስቀድሞ ተገቢውን የጉምሩክ ቀረጥ በመክፈል የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብት ለሌለው ሰው ሊተላለፍ ይችላል፡፡

፪/ ባለሀብቱ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ያስገባውን የካፒታል ዕቃ ወይም የግንባታ ዕቃ ከቀረጥና ታክሱ ነፃ ሆኖ መልሶ ከአገር እንዲወጣ ማድረግ ይችላል፡፡

23. Exemption of Motor Vehicles from Customs Duty

1/ The Ministry shall, based on the type and nature of investment projects, submit proposals to the Investment Board for the duty and tax-free importation of cargo, public transport, and special-purpose vehicles intended for investment purposes.

2/ Upon approval of the proposal by the Board pursuant to Sub-Article (1) of this Article, the Ministry shall issue a directive determining the conditions under which vehicles may be imported free from customs duties and tax incentives.

24. Transfer of Goods Imported with Customs Duty and Tax Incentives

1/ Capital goods or construction materials imported with customs duty and tax incentives may be transferred, upon payment of the applicable customs duties, to persons who do not possess similar privileges.

2/ The investor may re-export capital goods or construction materials that were imported with customs duty and tax incentives.

፫/ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ መብት ላለው ሰው ሊተላለፍ ይችላል፣ ዝርዝር አፈጻጸሙ ሚስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

ክፍል አምስት

የማዕድን፤ ነዳጅ እና የጂኦተርማል ሥራዎች

፳፭. ለማዕድን ኢንቨስትመንት የሚሰጥ ማበረታቻ

፩/ የማዕድን ስራዎች፡-

ሀ) ማንኛውም የምርመራ ባለፈቃድ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ለስራው የሚያስፈልጉና በጸደቀው የስራ ፕሮግራም መሰረት ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው መሳሪያዎች፣ የግንባታ ዕቃዎች፣ ማሽነሪዎች እና አላቂ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናሉ፤

3/ Goods imported benefiting from customs duty and tax incentives may be transferred to a person who has similar right to customs duty and tax incentives. The detailed implementation shall be determined by a Directive to be issued by the Ministry.

PART FIVE

MINING, PETROLEUM AND GEOTHERMAL WORKS

25. Incentive for Mining Investment

1/ Mining works:

a) Any holder of an exploration license or its contractor may import into Ethiopia equipment , machinery and consumables required for its operations, in accordance with the approved work program, with customs duty and tax incentives by way of customs duty and tax incentives;

ለ) ማንኛውም የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ለስራው የሚያስፈልጉና በጸደቀው የስራ ፕሮግራም መሰረት ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው የማምረት ስራውን ለመጀመር የሚያስችሉ መሳሪያዎች፣ የግንባታ ዕቃዎች፣ ማሽነሪዎች እና አላቂ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናሉ፤

b) Any holder of a small -scale or large -scale mining license or its contractor may import into Ethiopia equipment, machinery and consumables required to commence Mining Operations, in accordance with the approved work program, with customs duty and tax incentives by way of customs duty and tax incentives;

ሐ) የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ የምርት ስራውን በላቀ ደረጃ ለማስፋፋት ሲፈልግና የማስፋፊያው ዕቅድ በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ሲጸድቅ ለማስፋፊያ ስራው የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን ፣ የግንባታ ዕቃዎችን፣ ማሽነሪዎችን እና አላቂ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ማስገባት ይችላል፤

c) A holder of a Small -Scale or Large -Scale Mining license who undertakes a major expansion of mine production shall have the right to import, with customs duty and tax incentives equipment, machinery and consumables necessary for the expansion, provided that the expansion program has been approved by the Regulatory Institution;

መ) የባህላዊ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ወይም አሸዋ፣ ገረጋንቲ፣ ጠጠር እና የመሳሰሉትን ለማምረት የሚያስችል ፈቃድ ያለው ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ ንዑስ አንቀፅ ተራ ፊደል (ሀ) (ለ) እና (ሐ) የተመለከቱት የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብት ተጠቃሚ አይሆንም፤

d) Any holder of an artisanal mining license or a holder of any construction material mining license issued for the mining of sand or selected materials shall not be entitled to customs duty and tax incentives under (a), (b), and (c) of this Sub Article;

ሠ) የልዩ አነስተኛ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ለስራው የሚያስፈልጉና በተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ በጸደቀው መሰረት ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው የማምረት ስራውን ለማከናወን የሚያስችሉ መሳሪያዎችን እና ማሽነሪዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናል፣

e) The holder of a Special Small-Scale Mining license shall benefit from customs duty and tax incentives for equipment and machinery imported, as required for its operations and approved by the Regulatory Authority;

ረ) የማዕድን ምርመራ ስራ ባለፈቃድ ለማዕድን ስራው አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ለመሰብሰብ የሚያስፈልግ አውሮፕላን፣ ሄሊኮፕተር፣ ድሮን ወይም ሌሎች ለስራው አግባብነት ያላቸው የመመርመሪያ መሳሪያዎች በተቆጣጣሪው ባለስልጣን አስፈላጊነታቸው ሲረጋገጥ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል፣

f) The holder of a mining license may import, with customs duty and tax incentives, Aircraft, Helicopters, Drones or other exploration equipment for the purpose of collecting relevant information for Mining activities, upon obtaining their necessity is verified by the Regulatory Authority;

ሰ) ማንኛውም ባለፈቃድ የተፈቀዱለትን መሳሪያዎች እና ማሽነሪዎች በማዕድን ማምረት ቅድመ ዝግጅት ጊዜ ማስገባት ካልቻለ ማዕድን ማምረት ከጀመረ በኋላ እስከ ፭ (አምስት) ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ይችላል፡፡

g) Any holder of a mining license who is unable to import equipment and machinery at the pre-development stage may import such goods, with customs duty and tax incentives, within 5 (Five) years from the commencement of production.

፪/ በማዕድን ዋጋ ላይ ተጨማሪ እሴት ማከል፡-

ሀ) ማንኛውም የመቅረፅ ዕደ ጥበብ ባለፈቃድ ወይም የማጣራት ባለፈቃድ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ የማዕድን ምርት የሚያመርት ከሆነ በጸደቀው የስራ ፕሮግራም መሰረት ለስራው ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው መሳሪያዎች እና ማሽነሪዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ማስገባት መብት ጸንቶ የሚቆየው ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ለ፫ (ሦስት) ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡

፫/ የነዳጅ፣ የተፈጥሮ ጋዝ እና የጂኦተርማል ስራዎች፡-

ሀ) ማንኛውም የምርመራ ባለፈቃድ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ለስራው የሚያስፈልጉና በጸደቀው የስራ ፕሮግራም መሰረት ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው መሳሪያዎች፣ የግንባታ ዕቃዎች፣ ማሽነሪዎች እና አላቂ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናሉ፤

2/ Value Addition in Mining:

a) Any holder of a handicraft license or a refinery license who is engaged in the export of minerals may import equipment and machinery required for its operations, in accordance with the approved work program, with customs duty and tax incentives.

b) Notwithstanding the provisions of paragraph (a) of this Sub Article, the privilege to import goods with customs duty and tax incentives shall remain valid only for 3 (Three) years from the date of issuance of the license.

3/ Petroleum , Natural gas and Geothermal works ፡

a) Any holder of an exploration license or its contractor may import into Ethiopia equipment , construction materials, machinery and consumables required for its operations, in accordance with the approved work program, benefiting from customs duty and tax incentives;

ለ) ማንኛውም የነዳጅ ወይም የጂኦተርማል ማምረት ባለፈቃድ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው የቁፋሮ፣ የጂኦሎጂካል፣ የጂኦፊዚካል፣ የማምረቻ፣ የማዘጋጃ፣ የማጣሪያ፣ ማጓጓዣ እና ሌሎች ለነዳጅ ስራዎች አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችና ዕቃዎች፣ የአየር፣ የባሕር መጓጓዣዎችን እና ሌሎች የመጓጓዣ መሳሪያዎችንና መለዋወጫቸውን ጨምሮ ለስራው ማስፈፀሚያ የሚያስፈልገውን ነዳጅ፣ ኬሚካሎች፣ ዘይት፣ ቅባትና መለዋወጫዎች፣ ፊልሞች፣ ሳይዝሚክ ቴፖች፣ ተንቀሳቃሽ ቤቶች፣ ተንቀሳቃሽ ቢሮዎችና ተገጣጣሚ ስትራክቸሮች የተፈታቱ ክፍሎች እና ለነዳጅ ስራ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ቁሳቁሶች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናሉ።

፬/ በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ቢኖርም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ ስትራቴጂክ ለሆኑ እና ለእሴት ጭማሪ አጋዥ ለሆኑ የማዕድን ወይም የነዳጅ ምርቶችና ሥራዎች ተጨማሪ ማበረታቻ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

b) Any holder of a petroleum or geothermal license or its contractor shall be entitled to import into Ethiopia all drilling, geological, geophysical, production, treating, processing, transportation and other machinery and equipment necessary for petroleum and geothermal operations , including aircraft , Maritime transportation, and other transportation equipment and parts thereof, as well as fuels, chemicals, oil, lubricants and accessories, films, seismic tapes, house trailers, office trailers and disassembled prefabricated structures and other materials necessary for petroleum and geothermal operations, benefiting from customs duty and tax incentives.

4/ Notwithstanding the provisions of this Article, the Ethiopian Investment Board may grant additional incentives for mining or petroleum products and activities that are strategic and conducive to value addition.

፭/ የባዮፊዩልን ጨምሮ አማራጭ ሙቀታዊ የኢነርጂ ምንጮች፡-

ሀ) ባዮፊልን ጨምሮ አማራጭ የሙቀታዊ ኢነርጂ ምንጮች ልማት ባለፈቃድ እንደፈቃዱ ዓይነት በጸደቀው የስራ ፕሮግራም መሰረት ለስራው የሚያስፈልጉ ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው መሳሪያዎችና ማሽነሪዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናሉ፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ የማስገባት መብት ጸንቶ የሚቆየው ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ለ፭ (አምስት) ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡

፮/ ለዚህ የደንቡ ክፍል አፈጻጸም "**አላቂ ዕቃ**" ማለት ለማዕድን፤ ለነዳጅ እና ለጂኦተርማል ስራዎች የሚያስፈልግ ኬሚካል፤ ድማሚት እና ሌሎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚዘረዝራቸው ዕቃዎች ናቸው፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ መሰረት በባለሀብቱ እና በተቆጣጣሪው ባለስልጣን መካከል የሚገቡት ስምምነቶች ወይም የስራ ፕሮግራሞች ከመጽደቃቸው በፊት በጉምሩክ አዋጁ በተደነገገው መሰረት ሚኒስቴሩ አስተያየት ሊሰጥበት ይገባል፡፡

5/ Alternative Thermal Energy Sources, including Biofuels:

a) The holder of a license to develop alternative thermal energy sources, including biofuels, shall benefit from customs duty and tax incentives for equipment and machinery imported as required for the work, in accordance with the approved work program;

b) Notwithstanding paragraph (a) of this Sub-Article, the privilege to import goods with customs duty and tax incentives shall remain valid for 5 (Five) years from the date of issuance of the license.

6/ For the purposes of this Part of the Regulation, "**consumables**" means chemicals, dynamite, and other materials to be used for mining, petroleum and geothermal activities as specified in a Directive issued by the Ministry.

7/ For the purposes of this Article, and in accordance with the Customs Proclamation, an opinion shall be submitted to the Minister before agreements or work programs between the investor and the Regulatory Authority are approved.

ክፍል ስድስት

የታክስ ማበረታቻዎች አስተዳደር

፳፮. የአፈጻጸም ስምምነት

፩/ አግባብነት ያለው የኢንቨስትመንት ተቋም በዚህ ደንብ መሰረት የታክስ ማበረታቻ በተፈቀደበት የኢንቨስትመንት መስክ ከሚሰማሩ ባለሀብቶች ጋር የአፈጻጸም ስምምነት ይፈራረማል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚፈረመው የአፈጻጸም ስምምነት የኢንቨስትመንቱን ደረጃ የካፒታል መጠን፣ የሚፈጠረውን የስራ እድል ብዛት፣ የምርት መጠን፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ፕሮጀክቱ የሚከናወንበት አግባብ እና የመሳሰሉትን የአፈጻጸም መለኪያዎች የሚይዝ እና የሪፖርት አቀራረብ ስርአት የሚዘረጋ ሊሆን ይገባል።

፫/ በሌሎች ህጎች በተደነገገው መሰረት ባለሃብቱ አግባብ ካለው የመንግስት አካል ጋር የተፈራረመው ሌላ የአፈጻጸም ስምምነት ካለ ተጨማሪ የአፈጻጸም ስምምነት መፈራረም ሳያስፈልግ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱ የአፈጻጸም መለኪያዎችን ጭምር በስምምነቱ ውስጥ በማካተት አንድ ስምምነት እንዲፈረም ማድረግ ይቻላል።

PART SIX

ADMINISTRATION OF TAX INCENTIVES

26. Performance Agreement

1/ The relevant Investment Institution shall enter into a performance agreement with investors engaged in investment areas eligible for tax incentives under this Regulation.

2/ The performance agreement concluded pursuant to Sub Article (1) of this Article shall include performance indicators such as level of investment, amount of capital employed, number of jobs created, quantity of production, technology transfer, the manner of undertaking the project and other applicable performance indicators and shall establish a reporting and monitoring system.

3/ Where an investor has to enter into a performance agreement with a competent government authority pursuant to other laws the performance indicators referred to under this Article may be incorporated into that agreement and a single agreement shall govern performance obligations without the need to sign an additional agreement.

፬/ የአፈጻጸም ስምምነቱ ግብር ከፋዩ በገባው ግዴታ መሰረት ባይፈጽም መንግስት ማበረታቸውን ቀሪ ማድረግ የሚችል መሆኑን የሚገልጽ መሆን አለበት።

፭/ ሚኒስቴሩ ሞዴል የአፈጻጸም ስምምነት ያዘጋጃል፣ ይህ ስምምነትም የአፈጻጸም ስምምነቱ ይዘት ባለሃብቱ በአፈጻጸም ስምምነቱ የገባውን ግዴታ አልተወጣም የሚባልባቸውን ሁኔታዎች እና የሚያስከትለውን ውጤት የሚዘረዝር ሊሆን ይገባል።

፳፯. <u>በጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ማበረታቻ ወደ አገር አገር በገቡ ዕቃዎች ላይ ስለሚደረግ ቁጥጥር</u>

፩/ በዚህ ደንብ መሠረት የግንባታ ዕቃዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ወደ አገር ውስጥ እንዲያስገባ የተፈቀደለት ባለሀብት የግንባታ ዕቃዎቹ ለታለመው ዓላማ የዋሉ መሆኑን የሚያስረዳ የግንባታ ፈቃድ በሰጠው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተረጋገጠ ማስረጃ ለተቆጣጣሪው መስሪያ ቤት በየ፫ (ሦስት) ወሩ ማቅረብ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተጠቀሰው ወደ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ለሚገቡ የግንባታ እቃዎች ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

4/ The performance agreement shall stipulate that the Government may suspend the incentive where the taxpayer fails to fulfill Obligations thereunder.

5/ The Ministry shall prepare a model performance agreement, which shall specify the content of the agreement, the circumstances under which an investor is deemed to have failed to fulfill its Obligations, and the consequences of such failure.

27. <u>Oversight of Goods Imported Under Customs Duty and Tax Incentives</u>

1/ An investor permitted to import construction materials into the country with the benefit of customs duty and tax incentives under this Regulation shall submit every 3 (Three) months, a certificate issued by the government authority that issued the construction permit confirming that the construction materials have been used for their intended purpose.

2/ Sub Article (1) of this Article shall not apply to the construction materials entering Special Economic Zones.

፫/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ማበረታቻ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የግንባታ እቃዎችን አይነት፣ ሊቀርቡ የሚገባቸውን ማስረጃዎች ዝርዝር እና ለየትኛው አካል መቅረብ እንዳለባቸው የሚወስን መመሪያ ያወጣል።

፬/ በዚህ ደንብ መሰረት የካፒታል ዕቃዎችን፣ የግንባታ ዕቃዎችን እና ተሽከርካሪዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ወደ አገር እንዲያስገባ የተፈቀደለት ባለሀብት የካፒታል ዕቃዎቹ፣ የግንባታ ዕቃዎቹ እና ተሽከርካሪዎቹ ለታለመላቸው ዓላማ የዋሉ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ለጉምሩክ ኮሚሽን ሲጠየቅ ማቅረብ አለበት፡፡

፳፰. የተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች የወል ተግባርና ኃላፊነት

ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች፡-

፩/ ባለሀብቱ የገቢ ግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ መሆን እንዲችል ለሚኒስቴሩ የሚከተለውን ማረጋገጫ ይሰጣሉ፡-

ሀ) ባለሀብቱ የንግድ ፈቃድ አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ ስለመሆኑ፤

ለ) ባለሀብቱ ምርት ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት የጀመረበትን ጊዜ፡፡

3/ The Ministry shall issue a Directive prescribing the type of Construction materials, list of evidence required to be submitted pursuant to Sub Article (1) of this Article and the persons responsible for providing such evidence.

4/ An investor permitted to import capital goods, construction materials and vehicles into the country with the benefit of customs duty and tax incentives under this Regulation shall upon request, provide evidence to the Customs Commission demonstrating that the capital goods, construction materials and vehicles have been used for their intended purpose.

28. Common Duties and Responsibilities of Regulatory Institutions

The Regulatory Institutions :

1/ Confirm to the Ministry, to enable the investor to be eligible for income tax incentives:

a) That the investor has obtained a business license and commenced operations;

b) The date on which production or the rendering of services commenced by the investor.

፪/ በዚህ ደንብ መሠረት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ የሚፈቀድለት ባለሀብት ወደ አገር ውስጥ ሊያስገባቸው የሚችሉ ለኢንቨስትመንቱ አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎች ዝርዝር በሚመለከት ለሚኒስቴሩ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባሉ፤

፫/ ለኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ብቁ የሚሆኑ የኢንቨስትመንት መስኮች በሚመረጡበት ጊዜ ሃሳብ ይሰጣሉ፤

፬/ ለባለሀብቱ የተሰጠውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ እና የተገኘውን ጥቅም በተለይም የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በማሳደግ ረገድ እያንዳንዱ ባለሀብት ለአገሪቱ ያስገኘውን ጥቅም የሚያሳይ ሪፖርት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ፫ (ሦስት) ወር ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ያቀርባሉ፤

፭/ የተሰጣቸውን የታክስ ማበረታቻ ከተፈቀደበት አላማ ውጪ ተጠቅመው የተገኙ ባለሃብቶችን የሚመለከት መረጃ ሲኖራቸው ይህንኑ እንደ አግባብነቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር፣ ለታክሱ ባለስልጣን ወይም ለጉምሩክ ኮሚሽን ያስታውቃሉ።

፳፱. የኢንቨስትመንት ተቋማት ተግባር እና ኃላፊነት

የዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፰ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የኢንቨስትመንት ተቋማት የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፡-

2/ Submit to the Ministry proposals regarding investor the list of equipment required for investment operations that may be imported with customs duty and tax incentives;

3/ Participate in the formulation of standards and eligibility criteria for tax incentives;

4/ Submit quarterly reports to the Ministry specifying investment incentives and the benefit obtained specially creation of job opportunity, increasing foreign currency gain regarding each investor provide benefit for the country;

5/ Where information indicates that a taxpayer has used incentives for purposes other than those authorized, report such information, as appropriate, to the Ministry of Finance, the Tax Authority, or the Customs Commission.

29. Duties and Responsibilities of Investment Institutions

Without prejudice to Article 28 of this Regulation, the Investment Institutions shall have the following duties and responsibilities:

፩/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጧቸው ባለሀብቶች በዚህ ደንብ መሠረት፣

ሀ) በተዘረጋው የኢሌክትሮኒክ ስርአት አማካኝነት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ለመሆን የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ይቀበላሉ፤ የማበረታቻ ጥያቄው አግባብት ካለው ሕግ ጋር የተጣጣመ መሆኑን እና የሚቀርቡ ሰነዶችን ትክክለኛነት በመመርመር ያረጋግጣሉ፤ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለሚኒስቴሩ ያስተላልፋሉ፤

ለ) የገቢ ግብር ማበረታቻ ተጠቃሚ ለመሆን በተዘረጋው ስርዓት አማካኝነት የሚያቀርቡትን ማመልከቻ ይቀበላሉ፤ የማበረታቻ ጥያቄው አግባብነት ካለው ሕግ ጋር የተጣጣመ መሆኑን እና የሚቀርቡ ሰነዶችን ትክክለኛነት በመመርመር ያረጋግጣሉ፤ በዚህ ደንብ አንቀፅ ፳፮ መሰረት ከባለሀብቱ ጋር ተገቢውን የአፈጻጸም ስምምነት በመግባት ከድጋፍ ደብዳቤ ጋር ለውሳኔ ለሚኒስቴሩ ያስተላልፋሉ።

1/ In accordance with this Regulation the investors who have investment license,

a) Receive applications, through the single-window system developed, for customs duty and tax incentives privilege from investors who have obtained investment licenses; verify that the application complies with applicable laws and that supporting documents are accurate; and forward the application with recommendations to the Ministry for approval;

b) Receive applications for income tax incentives from investors through the system developed; verify consistency with Directives issued by the Ministry and Article 26 of this Regulation; conclude a performance agreement with the investor; and transmit the application with recommendations to the Ministry for approval.

፪/ አግባብነት ባለው ሕግ እና መመሪያ መሰረት የካፒታል እና የግንባታ ዕቃዎችን እና ተሽከርካሪዎችን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆኖ ወደ አገር ውስጥ እንዲያስገባ የተፈቀደለት ባለሀብት ዕቃዎቹን ለታለመላቸው ዓላማ ያዋለ መሆኑን ለመቆጣጠር በመስክ ምልከታ፣ በሪፖርት፣ ተቆጣጣሪ በመመደብ ወይም በሌላ ማናቸውም ዘዴ ተከታታይነት ያለው ክትትል ያካሂዳል፤ በየአመቱም ለሚኒስቴሩ የተጠቃለለ የአፈጻጸም ሪፖርት ይልካል፡፡

፫/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፮ መሰረት ባለሀብቱ በገባው የአፈጻጸም ስምምነት መሰረት የአፈጻጸም መለኪያዎቹ የተሟሉ መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችል የሪፖርት አቀራረብ ስርአት ይዘረጋል።

፬/ ባለሀብቱ በአፈጻጸም ስምምነቱ በገባው ግዴታ መሰረት የአፈጻጸም ስምምነቱን ሳይፈጽም የቀረ መሆኑን ሲያረጋግጥ የተሰጠው የገቢ ግብር እና የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ቀሪ እንዲሆን ለሚኒስቴሩ የውሳኔ ኃሳብ ያቀርባል።

2/ Through field inspections, reports, assignment of supervisors, or other appropriate means, ascertain that investors granted customs duty and tax incentives privileges for the importation of capital goods and building materials, and Vehicles have used such goods for the designated purposes, and submit annual consolidated reports to the Minister.

3/ In accordance with Article 26 of this Regulation, establish a reporting system to ensure that performance indicators are met under the performance agreement.

4/ Where the investor has failed to fulfill obligations under the performance agreement, submit a proposal to the Ministry recommending suspension of the income tax, customs duty, and tax incentives granted.

፴. የታክሱ ባለስልጣን ተግባር እና ኃላፊነት

የታክሱ ባለስልጣን፡-

፩/ የተፈቀደው የገቢ ግብር ማበረታቻ አግባብነት ካለው ህግ ጋር የተጣጣመ መሆኑን በማረጋገጥ የገቢ ግብር ማበረታቻውን ተፈፃሚ ያደርጋል፤

፪/ የገቢ ግብር ማበረታቻ የተሰጣቸውን ባለሀብቶች ዝርዝር፣ የተሰጣቸውን የማበረታቻ ተፈፃሚ የሚሆንበትን የጊዜ ርዝመት እና የሚያበቃበትን ጊዜ የሚያሳይ መዝገብ ይይዛል፤

፫/ በዚህ ደንብ መሠረት በተሰጠው የገቢ ግብር ማበረታቻ ምክንያት የታጣውን የገቢ ግብር የሚያሳይ መዝገብ ይይዛል፤

፬/ ከሌሎች መካከል፣ የገቢ ግብር ማበረታቻ የተሰጣቸውን ባለሀብቶች ዝርዝር፣ የተሰማሩበትን የኢንቨስትመንት መስክ እና ለባለሀብቶች በተሰጠው የገቢ ግብር ማበረታቻ ምክንያት የታጣውን ገቢ የሚያሳይ ሪፖርት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ፪ (ሁለት) ወር ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

፴፩. የጉምሩክ ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር

የጉምሩክ ኮሚሽን፡-

፩/ የተፈቀደው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር የተጣጣመ መሆኑን በማረጋገጥ ዕቃዎች በተሰጠው ማበረታቻ መሰረት ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል፤

30. Duties and Responsibilities of the Tax Authority

The Tax Authority shall:

1/ Implement the income tax incentive after ascertaining that it is consistent with relevant laws;

2/ Maintain records showing the investors granted income tax incentives, the duration of such incentives, and the date of termination of the tax incentives;

3/ Maintain records showing income tax forgone due to deviations from the standard income tax rate pursuant to this Regulation;

4/ Submit to the Ministry an annual report within 2 (two) months after the close of the fiscal year, indicating, among other details, the list of eligible investors, their investment areas, and the amount of tax forgone.

31. Duties and Responsibilities of Custom Commission

The Custom Commission shall:

1/ Permit the entry of goods with customs duty and tax incentives where such entry is consistent with applicable laws and the incentives granted;

፪/ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ የተፈቀደላቸውን ባለሀብቶች ዝርዝር፣ የተሠማሩበትን የኢንቨስትመንት መስክ እና የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆነው ወደ አገር ውስጥ የገቡትን ዕቃዎች ዋጋ እና የታላውን ገቢ የሚያሳይ መዝገብ ይይዛል፤

፫/ ባለሀብቶች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆነው ወደ አገር ውስጥ ያስገቧቸው ዕቃዎች ለታለመላቸው ዓላማ የዋሉ መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችል መደበኛ ክትትል እንዲሁም የድህረ ኦዲት ተግባር ያከናውናል፤

፬/ ባለሀብቶች በጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ወደ አገር ውስጥ ያስገቧቸውን ዕቃዎች ለታለመለት ዓላማ ያላዋሉ መሆኑ በመደበኛው አሰራርም ሆነ በኦዲት ሲረጋገጥ ጸንተው በሚሠራባቸው ሕጎች መሠረት ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤

፭/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተከናወኑ ተግባራትን የሚያሳይ የሩብ አመት ሪፖርት የሩብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በ፴ (ሠላሳ) ቀናት ጊዜ እንዲሁም ዓመታዊ ሪፖርት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ፪ (ሁለት) ወር ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

2/ Maintain records showing the list of investors granted customs duty and tax incentives, the investment areas involved and the value of goods imported with customs duty and tax incentives , and the corresponding tax forgone;

3/ Conduct post-clearance audit and regular monitoring to ascertain that goods imported with customs duty and tax incentives are used for their intended purposes ;

4/ Take legal measures in accordance with applicable laws where by Regular Procedure also post -audit findings confirm misuse of with customs duty and tax incentives goods under incentive scheme for unintended purposes;

5/ Submit quarterly reports to the Minister within 30 (Thirty) days of each quarter’s end, and annual reports within 2 (Two) months after the end of the fiscal year, detailing activities undertaken pursuant to this Article.

፴፪. የገንዘብ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

የገንዘብ ሚኒስቴር፡-

፩/ የዚህን ደንብ ዓላማ የሚያሳካ እና በቂ የኢኮኖሚ ምክንያት መኖሩን ሲያምንበት ማበረታቻ በሚያስፈልገው እና በዚህ ደንብ ከተመላከተው ውጭ በሌሎች የኢንቨስትመንት መስኮች የሚሰማሩ ባለሀብቶች ተገቢውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ እንዲያገኙ በመመሪያ ሊፈቀድ ይችላል፤

፪/ በዚህ ደንብ መሰረት ለማበረታቻ ብቁ ለሆነ ኢንቨስትመንት የተሰጠውን የገቢ ግብር ማበረታቻ ወይም የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ የሚያስገኝ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ይሰጣል፤

፫/ ባለሀብቶች የተሰጣቸውን የኢንቨስት መንት ማበረታቻ ለማስፈጸም አግባብነት ባለው የተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት ላይ ያለውን ቅሬታ ይቀበላል፣ ተገቢውን ትብብር እና ክትትል በማድረግ ባለሀብቱ ለገጠመው ችግር እልባት እንዲሰጠው ያደርጋል፤

32. Duties and Responsibilities of Ministry of Finance

The Ministry of Finance:

1/ Where the incentive is deemed to achieve its objectives of this Regulation and there is sufficient economic justification, permit by Directive the granting of investment incentives to investors engaged in investment activities not specified in this Regulation;

2/ Grant tax incentives to investments eligible under this Regulation, including income tax incentives or customs duty and tax incentives;

3/ Receive, coordinate and follow complaints submitted by investors on Regulatory Institution regarding the implementation of granted incentives and ensure appropriate resolution;

፬/ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለመስጠት የሚያገለግሉ ተጨማሪ መስፈርቶችን፣ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ ሆነው ወደ አገር ሊገቡ ወይም ከአገር ውስጥ ሊገዙ የሚችሉ ዕቃዎችን ዝርዝር፣ የእነዚህ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ተጠቃሚ ለመሆን ጥያቄ የሚያቀርቡ ባለሀብቶች ሊያቀርቧቸው የሚገባ ሰነዶችን የሚያሳይ መመሪያ ያወጣል፤

4/ Issue Directives establishing additional criteria for eligibility, the list of items that may be imported with customs duty and tax incentives or purchased locally and the documentation required to qualify for such privileges;

፭/ እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለታለመለት ዓላማ የዋለ መሆኑን በማረጋገጥ ረገድ ያከናወነውን ተግባር በመደበኛ ሁኔታ ይቆጣጠራል፤

5/ Monitor regularly the performance of regulatory institutions to ensure that tax incentives are used for their designated purposes;

፮/ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ በመሰጠቱ ምክንያት የታጣውን ገቢ ያጠቃልላል፣ የተጠቃለለውን ሂሣብ እና የኢንቨስትመንት ማበረታቻው በመሰጠቱ ምክንያት የተገኘውን ጥቅም የሚያሳይ ሪፖርት በዓመታዊ የመንግሥት የሂሣብ ሪፖርት ውስጥ በማካተት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ በየዓመቱ ይህንን ሪፖርት አትሞ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፤

6/ Consolidate forgone revenue and report to the House of Peoples' Representatives the value of tax forgone and the benefits derived from granting such privileges and publish such report annually;

፯/ የተፈቀደውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ መተንተን እና መቆጣጠር የሚያስችል የመረጃ ቋት ያደራጃል፤

7/ Maintain a database for monitoring and analysis of investment incentives granted ;

፰/ የተሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን ለመቆጣጠር እና ግልጽ ለማድረግ የሚያስችል በዘርፍ እና በኢንዱስትሪ ደረጃ የሚከተሉትን መረጃዎች ይይዛል፡-

ሀ) ለተመዘገቡ ባለሀብቶች የተሰጠውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ፤

ለ) ለቀጣይ የበጀት ዓመት ባለሀብቶች ሊያቀርቡ ይችላሉ ተብሎ የሚገመተውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ጥያቄ፤

ሐ) በተያዘው የበጀት ዓመት ሊፈቀድ ይችላል ተብሎ በዕቅድ የተያዘውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ፤

መ) ለቀጣይ የበጀት ዓመት ሊፈቀድ ይችላል ተብሎ የታቀደውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ፤

፱/ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚኖረውን ውጤት ለማወቅ እንዲቻል የተሰጠውን ማበረታቻ እና በማበረታቻው ምክንያት የተገኘውን ጥቅም የሚያሳይ ትንታኔ ያከናውናል፡፡

8/ The investment incentives provided For the purpose of monitoring and transparency, maintain the following sectorial and industry-level data on:

a) Investment incentives granted for Registered investors;

b) The investors Estimated incentive claims in the year preceding the current year

c) The programmed tax incentives for the current year;

d) Projected incentives for the following year;

9/ Conduct a cost–benefit analysis on investment incentives to assess the impact of tax incentives on the national economy.

ክፍል ሰባት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፴፫. የታክስ ማበረታቻን ቀሪ ስለማድረግ

፩/ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የተሰረዘበት ባለሀብት የወሰደውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ እንዲመልስ ይደረጋል፡፡

፪/ ያለአግባብ የተወሰዱ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች የሚመለሱበት ሁኔታ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፴፬. ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነትን ባለመወጣት ስለሚጣል መቀጫ

፩/ ማናቸውም የመንግሥት ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ በቂ ምክንያት ሳይኖረው በዚህ ደንብ በተደነገገው መሠረት ስለታክስ ማበረታቻዎች አፈፃፀም ሊያቀርብ የሚገባውን ሪፖርት ወይም መረጃ ያላቀረበ እንደሆነ ፀንተው በሚሠራባቸው ሕጎች መሠረት በወንጀል ወይም በአስተዳደር የሚኖርበት ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ እስከ ፫ (ሶስት) ወር የሚደርስ ደመወዝ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጣለውን የገንዘብ መቀጫ የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

PART SEVEN

MISCELLANEOUS PROVISIONS

33. Revocation of Tax Incentives

1/ An Investor whose investment license is revoked shall return all investment incentives acquired.

2/ The Ministry shall issue a directive determining the procedures for reclaiming improperly acquired incentives.

34. Penalty due to Failure to Submit Reports

1/ Without prejudice to criminal or administrative liability under applicable laws, any government official or employee who, without good cause, fails to submit reports required under this Regulation shall be subject to a fine of up to 3 (Three) months' salary.

2/ The Ministry is authorized to impose and collect the fine provided under Sub Article (1) of this Article.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ደንብ በተደነገገው መሰረት የሚጠበቀውን ያለፈውን ዓመት ሪፖርት ያላቀረበ የኢንቨስትመንት ወይም የማዕድን መስሪያ ቤት ሪፖርቱ እስከሚቀርብ ድረስ ለሚኒስቴሩ የሚልካቸው የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ጥያቄዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡ ሆኖም ሪፖርቱ ከቀረበ ጊዜ ጀምሮ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ጥያቄዎች መስተናገድ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

፴፭. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ሚኒስቴሩ ለዚህ ደንብ አፈፃፀም የሚያግዙ መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

፴፮. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

፩/ የተሻሩትን የኢንቨስትመንት ማበረታቻና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ የሥራ መስኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር (እንደተሻሻለ) ፪፻፸/፪ሺ፭ እና የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር ፭፻፲፯/፪ሺ፲፭ (በደንብ ቁጥር ፭፻፷፮/፪ሺ፲፮ እንደተሻሻለ) መሠረት በማድረግ የተሰጡ ማበረታቻዎች የተሰጠው የታክስ ማበረታቻ ጊዜ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

3/ Notwithstanding the provisions of Sub Articles (1) and (2) of this Article, where an investment or mining office fails to submit the annual report for the preceding year as required under this Regulation, any application submitted to the Ministry for investment incentives shall not be processed and shall be deemed rejected until such report is duly submitted. Upon submission of the required report, the processing of the investment incentive application shall recommence as of the date of submission.

35. <u>Power to Issue Directives</u>

The Ministry may issue directives for the proper implementation of this Regulation.

36. <u>Transitional provisions</u>

1/ Tax incentives granted pursuant to the Investment Incentives and Investment Reserved for Domestic Investors Council of Ministers Regulation (as amended) No. 270/2012 and Investment Incentive Regulation No. 517/2022 (as Amended by Regulation No. 566/2025) shall remain valid until the expiration of the incentive period granted.

፪/ ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የወሰደ ባለሀብት የሚሰጠው ማበረታቻ ነባሩን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር (እንደተሻሻለ) ፭፻፲፯/ ፪ሺ፲፬ መሠረት ይሆናል፡፡ ሆኖም ባለሀብቱ በአዲሱ ማበረታቻ ደንብ መሰረት እንዲስተናገድ ሊመርጥ ይችላል፡፡

፫/ ይህ ደንብ ስራ ላይ ከዋለበት ቀን በፊት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ባጸደቃቸው የማዕድን፣ የነዳጅ፣ ጂኦተርማል፣ ባዮ ፊዩል እና የተፈጥሮ ጋዝ ስምምነቶች የተፈቀዱ ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የመሆን መብቶች በስምምነቶቹ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል።

፴፯. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር ፭፻፲፯/፪ሺ፲፩ (እንደተሻሻለ) በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፪/ በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር ፭፻፲፯/ፍሺ፲፩ (እንደተሻሻለ) መሰረት የወጡ መመሪያዎች ከዚህ ደንብ ጋር የማይቃረኑ እስከሆነ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል።

2/ An investor who obtained an investment permit before the issuance of this Regulation shall be granted incentives in accordance with the then existing Investment Incentives Regulation (as amended) No. 517/2022. However, the investor may opt to be treated under the new incentive Regulation.

3/ Exemptions from duties and taxes granted under mining, oil, geothermal, biofuel, and natural gas agreements approved by the Council of Ministers prior to the entry into force of this Regulation shall continue to apply until the end of the period determined by the agreement.

37. Repealed and Inapplicable Laws

1/ Council of Ministers Investment Incentive Regulation (as amended) No. 517/2022 is hereby repealed.

2/ The Directives issued pursuant to Investment Incentives Regulation (as amended) No. 517/2022 shall remain in force to the extent that they do not conflict with this Regulation.

፫/ ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ ደንብ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፴፰. <u>ደንቡ የሚጸናበት ቀን</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

አብይ አህመድ (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

3/ No Regulation, Directive, or practice inconsistent with this Regulation shall apply to matters covered herein.

38. <u>Effective Date</u>

This Regulation shall enter in to force on the date of its publications in the federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa , On this 23rd Day of February, 2026

ABIY AHMED (Dr.)
PRIME MINSTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA